## ከመጠምጠም መማር ይቅደም!

## ልብ ሳይገዙ ነገር አያበዙ !

ሚች ለሀቅ (ከመርካቶ)

ትግልና አሉባልታ ተቃቅፈው ሲሄዱ ያምራሉ፡፡ አቤት እግዚኦ ጉድ ያሰኛሉ፡፡ ዕድሜ ለአምባገኖቻችንና ለአብዮታዊ ዴሞክራሲያቸው ደግሞ በውስጥም በውጭም የውሸት ፋብሪካዎች በየቦታው ተቀፍቅፈውልናል። ለመነሻ ርዕስነት ደግሞ ጥቂትም ቢሆኑ አይታክቴዎች፣ ቃልኪዳናቸውን ሳያጥፉ የግንባር ሥጋ የሆኑባቸው ታጋይ መሪዎች ትላንትም ነበሩ፣ ዛሬም አሉ፣ ወደፊትም ይኖራሉ። ታዲያ ለሥጥ እንግዲሁ ምን ችግር አለው። ሥጥ እንግዲህ ያለገደብ ........... አቶ ኢያሱ በዋቢ ሸበሌ ሶሻሊስቱ ጠንቋይ የሚለው መፀሐፋቸው ሲመረቅ ተገኝተው መፈረማቸው ምን ያነጋግራል? በሚቹ መለስ መቃብር ቤት አይሉት ሀውልት ላይ የአበባ ጉንጉን አኑረዋል፡፡ በአዲስ አበባው የአሜሪካ ኤምባሲ በተደረገላቸው የእራት ግብዣ ላይ ስለ ምርጫ ፖለቲካ ታዳሚዎችን ያስጨበጨበ ንግግር አድርገዋል፡፡ በስብሀት ነጋ ቅምጥ መሸታ ቤት ከሞት እምቢው የእንጨት ሽበት ጋር የቮድካ መለኪያ ሲያጋጩ በዓይኔ በብሌኑ አይቻቸዋለሁ፡፡ በአዲስ አበባ ጀርመን ኤምባሲ አለም አቀፍ ፀረ-ሽብር ዘመቻን በተመለከተ በአሜሪካ መሪነት በዓለም ዙሪያ በሰላማዊ ህዝቦች ላይ የሚካሄደውን ዘግናኝ ጭፍጨፋ በመደገፍና እስራኤል በፍልስጤም አረጋውያን፣ ሴቶች፣ ህጻናት፣ አቅመ-ደካሞች ላይ እያደረሰች ያለችውን ጭፍጨፋ ፍትሀዊነትን መስክረዋል፡፡ አመጣጣቸው ምንም እንኳን በይፋ ባይገለጽም በወያኔ ምስረታ 40ኛ አመት ላይ ለመገኘትና ለድርጅቱ ያላቸውን አድናቆት ለመግለጽ መሆኑን ከወያኔ የውስጥ ሰዎች ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ታላቁ የአባይ ግድብን በጎበኙበት በጣሊያን ኢንጂነሮች የግድቡ አጠቃላይ ሁኔታ ሲገለጽላቸው በተመስጦ አድምጠዋል፡፡ በነገራችን ላይ የዛሬ ሦስት ወር አካባቢ በሐራሬ ከአረመኔው መንግስቱ ጋር ሮበርት ሙጋቤ በተገኙበት ሰፊ ውይይት አካሂደዋል፡፡ በረከትና ጓደኞቹ ለክብራቸው በካሌብ ሆቴል ባዘጋጁት ግብዣ ላይ በመገኘት የድርሻቸውን ብሉ ሌብል ጆኒ ዎከር ውስኪን ጋብዘዋቸዋል፡፡ ከሁሉም በላይ የሚያንገበግበው ድርጅታው ኢሕአፓን ሳያማክሩ ማሰባቸው ሳያንስ መጽሐፍት እያሳተሙና በተለያዩ ቋንቋዎች በማን አለብኝነት እየተተረጎሙ መቸብቸባቸው አስተዛዛቢ ሆኗል፡፡ ተርጉማ መጽሐፋቸው በሀገር ቤት እንዲሰራጭ ያደረገችው ወጣትም ታሪክ ይፋረዳታል። ከዋቢ ሸበሌ በኋላ ጎንደር ጥምቀትን አክብረው ከአላሙዲው ትንሽ አነስ በሚለው የግል ጄታቸው ወደ አስመራ አቅንተው ከሰዎቹ ተወያይተዋል። አዲስ አበባን አይቶ የማያውቀው የሻዕቢያ ባለስልጣን የማነ ገብረአብ፤ አብረው በአዲስ አበባብ ተምረው ቅርብ ጓደና ናቸውና ተወያተዋል። ኢስያስም የግንቦት 7 ጋዜጠኞችን በሚገነባው ግድብ አጠገብ ሲያገኛቸው፣ አቶ ኢያሱን ግን በደንብ ቤተ መንግስት ጋብዞ ቢያወያያቸውስ ምን

ያስገርማል? ....... ምን ችግር አለ። መርዘኛው ሥጥ እንግዲህ፣ ሰምቶ የሚመረዝ ጆሮ እስካለ ድረስ ይቀጥላል። በሁሉም ቦታ፣ በየምግብ ቤቱ፣ በየለቅሶ ቤቱ፣ በየሰርግ ቤቱ፣ በየሬዲዮኑ፣ በየስብሰባው...

በተመሳሳይ መልኩ ፋሽስቱ ደርግ ኢህአፓን የኢዲዩ ተቀጽላና የፊውዳል ወላጆቻቸው የኤኮኖሚ ጥቅም በመነካቱ የተሰማቸው ልጆቻቸው የመሰረቱትና ያረጀ ያፈጀውን የፊውዳል ሥርአት ለመመለስና አብዮቱን ለመቀልበስ የተቋቋመ አናርኪስት ድርጅት ነው በማለት ይከስ ነበር፡፡ በዚህም ሳይወሰን ምንም አንኳን ድርጅቱ ሲመሰረት ሻዕቢያ የተባለ ገና ባይመሰረትም በኤርትራ ተዋጊ ድርጅቶች በጀብሀና በሻቢያ የተመሰረተ እንደሆነም ማቅረቡ ያታወሳል፡፡ በሶርያ ይደገፍ እንደነበርና የፔትሮ ዶላር ቅጥረኛ እየተባለ ይዘለፍ እንደነበርም አይሳትም፡፡ ከሶማሌው አምባገነን መሪ ጋር በመነጋገር የሶማሌ ጦር አስተኳሽ እንደነበርም ዛሬ ድረስ ሽንጣቸውን ገትረው የሚሟገቱ ሰዎች ቁጥር ቀላል የሚባል አይደለም፡፡ ሌሎች ደግሞ ስልት አጥቶ ሲሶ ኢትዮጵያን የሶማሌ መሬት ብሎ በሶማሊያ እንደ ብልጡ ወያኔ ተረድቶ ለስልጣን ከመብቃት ፈንታ ድርቅ እምቢ ብሎ ከድል ራቀ ይላሉ። የጉደኛው ደርግ ካድሬዎች የኢምፔሪያሊስቶች ቅጥረኛ በማለትም ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያሳጡት መስሏቸው ይዘላብዱ እንደነበር አይዘነጋም፡፡ ጥቂት የድንጋይና የእንጨት ሽበት ልሂቃኖች ኢሕአፓ አላማው ለሀገርና ለሕዝብ ሳይሆን በተጻጻራሪው ለሥልጣን መሆኑን ያዙን ልቀቁን ያላሉ፡፡ ታዲያ ለህዝብ ስልጣን እንጂ የናተን መላጣ ሊያሻሽ ነው ቢባሉም አደብ አልገዙም። አንዳንዶቹም ሰፊ ጥናትና ምርምር አካሂደው የደረሱበት ጉዳይ የኢሕአፓ የሥልጣን ጥመኝነት መሆኑን በጽሑፍ ማቅረባቸውን በመስበክ ግዙና አንብቡ ሲሉ እግረ መንገዳቸውን የሽያጭ ማስታወቂያ ይሰራሉ። ያልነበሩ ቢሆንም የድርጅቱ አመራር አባል ነበርን፤ የማናውቀው ምስጢርም የለም ብለው ጉራ መቸርቸራቸው የተለመደ ሆኖ መርካቶንም ሊያስለቅቀን ነው።

በዚህ በዘረኛው የወያኔ ሃያ ሦስት አመት ዘመን በደርግ ዘመን ይባል የነበረው ተገልብጦ ሻብያን፣ ጀብሀን፣ ወያኔን የመሠረተው ኢሕአፓ እንደሆነ አቋቋሚ ነበርን እያሉ የሚዘላብዱ ጉዶች እንደ እንጉዳይ ፈሉ፡፡ ከዚህ ጋር አያይዘውም የዘር ፣ የብሔር ብሔረሰብ ፖለቲካን ሻዕብያንና ወያኔን ያስታጠቀ ኢሕአፓ እንደሆነ መረጃ ሳይቀር እንዳላቸው የሚቧችሩና የሚያጓሩ ጃስ የተባሉ ጡሩምባ ነፊዎች በረከቱ፡፡ ኢሕአፓ ከኢትዮጵያ የመገንጠል አላማ የትግላቸው የማዕዘን ድንጋይ አድርገው ከቆሙ ቡድኖች ጋር ፊት ለፊት ግንብር ለግንባር በመፋለሙና በእናት ሀገር ኢትዮጵያ ህልውና ላይ ምንም ዓይነት ድርድር ውስጥ እንደማይገባና ጉዳዩ ለድርድርም መቅረብ የሌለበት መሆኑን አበከሮ ጥርሱን ነክሶ ስለሚሟገትና ስለሚፋለም አባይ ኢትዮጲያ (ትልቋ ኢትዮጵያ) በማለት ይሳለቁበት እንደነበር ማስታወስ የግድ ይላል፡፡ ከቅርብ አመታት ወዲህ አክራሪ፣ አምባገነን፣ ግትር የመሳሰሉ የስም ማጥፊያ ጭቃዎች እየተለጠፉበት ይገኛል፡፡ ኢሕአፓ በኢትዮጵያ አንድነትና ሉአሏዊነት ላይ እንደማይልመጠመጥና ለአፍታም ከአቋሙ

ዘመም እንደማይል ደግሞ ደጋግሞ በመግለጽ ይህ አክራሪ ካሰኘ እሰየው ብሏል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ የፖለቲካ፣ የኤኮኖሚና ሌሎች ችግሮች የሚፈቱት ሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝቦች በሚያደርጉት የጋራ ትግል መሆኑን አበክሮ ያምናል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ የዴሞክራሲ ተመጽዋች ሳይሆን እራሱ የዴሞክራሲ ባለቤት ሲሆን እስከ ዛሬ የተጫኑትን ችግሮች በዴሞክራሲ ይፈታቸዋል የሚለው የኢሕአፓ የመሰረት ድንጋይ እንደማይናወጽ ደግሞ ደጋግሞ አስረግጦ ቢገልጽም በመቀመጫቸው ሳይሆን በጭንቅላታቸው የተቀመጡ ሁሉ አይገባቸውም አይረዱትም፡፡ ይህ የኢሕአፓ ችግር አይደለም፡፡ ኢሕአፓን አምባገነን የሚሉትም ኢሕአፓ በሀገር ህልውና እና በኢትዮጵያ ሕዝብ መብትና ነጻነት ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጀርባ ምንም አይነት መነናበስና ድርድር እንደማያደርግና ለማድረግም ባህርዩና የተጓዘባቸው የትግል ውጣ ውረዶች፣ ለክቡር፣ ለሕዝባዊ አላማ የተሰዉት ሰማዕታት ደምና አጥንት ስለሚወቅሰው ባለው አቅሙ እንዲህ ያለውን ተግባር ይቃወማል፡፡ ደግሞ ደጋግሞ ያወግዛል፡፡ ይህም አምባገነን የሚል ጭቃ ካስለጠፈበት ይቀበለዋል እንጂ ከሕዝበባዊ አቋሙ ውልፊት እንደማይል ለሁሉም በማይከብድ ቋንቋ ሳያሰልስ እየገለጸ ይገኛል፡፡ ኢሕአፓ በሀገር ሉአላዊነትና አንድነት ላይ አልደራደርም ማለቱን በአሁኑ ጊዜ ጠላት ሆነው ያጠቁትም እያመኑና ምስክርነትም እየሰጡ ናቸው። በአጭሩ በሀገር በኢትዮጵያ አንድነትና ሉአላዊነት፣ በኢትዮጵያ ሕዝብ ነጻነትና ህልውና ላይ አቋሙ ግትር ነው፡፡ ለሀገርና ለሕዝብ መቆም ግትር ካሰባለ አድምቃችሁ ጻፉት፣ ድምጽ ከፍ አርጋችሁ ጩሁት ከማለት ውጪ ምን ሊባል ይችላል?

በቅርቡ ወያኔ ወያኔ የሚሸቱ ድረ ገጾች በድርጅቱ ላይ ዘመቻውን አጧጡፈዋል። ሞት አፋፉ ያሉና የተጠሉ ዋሾና ነፍሰ ገዳዮችን ሳይቀር ለመድረክ እያቀረቡ ማስጮህን ተያይዘውታል። በግልባጩ ለፍርድ መቅረብ ያለባቸውን፤ በዜጎች ጥረትም ከተደበቁት አሜሪካና አውሮጳ ተቀፍድደው ቅጣታቸውን ለመቀበል ወደ ሀገር መላክ ያለባቸውም ቢሆኑ መድረክ ሰጥቶና አንቱ ብሎ ማዳነቅ ወንጀል መሆኑን የጠቀሰ አንድ ጋዜጠኛ የሚከተለውን ጥያቄና መልስ በቅርቡ ከሚመለከታቸው ጋር ያደረግ በመሆኑ ያገኘሁትን እስቲ ላካፍላችሁ።

*ጋዜጠኛ-- አንተ ልበልህና ምርመር አደራጊና ታሪክ ጸሃፊ ነኝ ብትልም ኢንሹራንስ አጭበርብረህ ድምጽህን አጥፍተህ ስትኖር ከርመህ አሁን ቡራ ከረዩ፤ ሀሰት መጠረቅና ኢሕአፓን መወንጀልን ምን አመጣው?*

*አቶ ዓይኔን በጨው-- በመጀመሪያ ደረጃ ድምጼን አላጠፋሁም። ማርያምን! ተችቼ ገምራው በምግታር ቢቀጣኝም፣ ሱባኤ መግባትን አልተውኩምና ነው። ሌላው ደግሞ ጥቃቱ በዛ ቀደም ሲል። ጓደኛዬ የነበረ ከድቶኝ ጉዴን ዘከዘከብኛና ለኢሕአፓ ጥቃት ተጋለጥኩ። ቀልቤሳን ካዩ ይጥነቀቁ ነው ጉዳዩ። በዚህ*

*መስከ ውንብድና  የተካነ ወዳጄ ተራ ሰነዶቹን ውድና ክቡር ብሎ በማቅረብ  የተከራየሁበት ቤት ውሃ አስገብቶ አጠፋበት በሚል ከሶልኝ ገንዘብ አስገኘኝና የነበርኩበትን ከተማ ጥዬ ለመሄድ ዕድል አገኘሁ።*

*ጋዜጠኛ-- ወደ መድረክ ለመመለስ ታዲያ ምን አነሳሳህ አሁን? በዝምታ መንቀዙና ሞትን መጠበቅ አይሻልህም ነበር?*

*ዓይኔን በጨው-- ምናልባት። አንተ እንዳልከው የሚሉኝ አሉ። ግን ዜና አቅራቢዎች ወሬ አጡ መሰለኝ አስቸገሩኝ።  ምርጫውም ተዳርሷል፤ ሰደትም ሰልችቶኛልና ጠሪ ካለ አለን አለን ማለት አይከፋም። ሌንጮን ከጠሩ እኔንስ ለምን ይተዉኛል? ሁለታችንም ለደርግ አግልግለናል፤ ሁለታችንም ሽግግር ሲሉ አቤት ብለን፤ አማራን ሰድበን እና የእነሱን የበላይነት ተቀብለን አገልግለናል። ወደእነሱ ጠጋ ለማለት ደግሞ ዋና ጠላታቸው የሆነውን ድርጅት ማውገዝ ያዋጣል ።*

*ጋዜጠኛ--በሀሰት መወንጀል?*

*ዓይኔን በጨው-- ታዲያ እውነቱን ተናግሬ ላመሰግናቸው ነው!? ከተቀደዱ አይቀር ይተርተሩ ነው መፈክሬ።*

*ጋዜጠኛ-- ለምን በኢሕአፓ ላይ ትኩረት?*

*ዓይኔን በጨው-- በዘመን ደርግ የነበረንን ዕድል ስላቃጠለብን። የዛሬዎቹ ደግሞ አጥብቀው ስለሚጠሉት፣ በሱ ላይ ማተኮሩ ሳያተርፍ አይቀርም።*

*ጋዜጠኛ-- የምርምርህ ውጤት የሆነ መጽሃፍ ከትበሃል?*

*ዓይኔን በጨው-- በርካታ ምዕራፎችን ጨርሺያለሁ። ስጨርስ አሳትመዋለሁ? ከቻልኩ እንደ ገብሩ አስራት በአሜሪካም በሀገር ቤትም።*

*ጋዜጠኛ-- ታዲያ በሰማኒያዎቹ የተጻፈ በአንተ ጌታ በደርግ ላይ ያተኮረ የስላቅ መጽሃፍ ወደ አማርኛ ተተርጉሞ በአዲስ አበባ ቢቀርብ ቢሸጥ ምን ችግር ወይ ጥፋት አለው?*

*ዓይኔን በጨው-- ምንም! ግን የአማራው ተረት እንደሚለው ማባበልና ማንቆሻበል፤ ማሞኘትና መደለል ቀላል እየሆነ መጥቷል። የአሉባልታ ሀይል ዘንድሮ ከባድ ነው። ሰዉ "አታሉኝ!? አሞኙኝ?!" ብሎ የሚለምን ይመስላል። ደራሲው ለወያኔ እጁን ሰጠ፤ መጽሀፉን ሊያስፈርም ፍንፍኔ ገባ፤ ከአባይ ጸሃይ ጋር ቆሞ አስፈረመ፤ ጉድ ጉድ ሲባል ይህንን በጽሁፍም በቃልም፤ በዋሺንግተነም በሎስ አንጀለስም ያስተጋቡ በዙ።  ወዲያውኑ ሌሎች ጮሌዎች ቀጠሉናም ደራሲው በጎንደር ጥምቀትን አከበረና በዚያውም አስመራ*

*ጎራ ብሎ ከኢሳያስ ጋር ዶለተ አሉ። ገበያው ደራ፤ ወያኔም እንደሰማሁት ከሆነ ፈንድቋል። ግለሰቡን የሚጠሉትና አንጃ ብሎ አሽቀነጠረን ብለው ነጥለው የሚከሱትም ዕልል አሉ። ይህ ነው እንግዲህ ቅንጣት የዕውነት መነሻን መሸፈኛ ሳይፈልግ ንጥር ያለ ውሸት ሆኖ ግን ብዙዎችን የሚያታልል። የውሸትና የአሉባልታ ወርቅ።*

*ጋዜጠኛ-- ሀሰት መሆኑ ሲጋለጥስ?*

*ዓይኔን በጨው--- ከንቱ! ሌላ ይፈልጋል--ሰዉ ሲዋሹትና ሲያጃጅሉት ዝም ብሎ ተቀባይ ከሆነ የውሸቱ ፋብሪካ አይዘጋም።*

*ጋዜጠኛ-- ወያኔ ለምርጫ ባይጠራህስ ? ወዲ ለታን ጠርቶ አንተን ቢዘጋህስ?*

*ዓይኔን በጨው --- እኔ ከሱ በምን አንሳለሁ?*

*ጋዜጠኛ - እንደው ለምናልባቱ ማለቴ ነው?*

*ዓይኔን በጨው-- በዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ወንጀል ዘረኝነት ብየ እከሳቸዋለሁ።*

*ጋዜጠኛ --- ፍርድ ቤቱ ክስህን ይቀበል ብለህ ታምናለህ?*

*ዓይኔን በጨው --- የተባበሩት መንግሥታት ፀሐፊው ባን ኪሞን ወዳጄ  ነው።*

*ጋዜጠኛ --- በምን ተገናኛችሁ?*

*ዓይኔን በጨው --- ስደት ላይ ብሆንም አባማም ሲችግረው ከሕግ ጋር በተያያዘ ጉዳይ በባን ኪሞን በኩል ምክር ጽፌ እንዲልክለት ይጠይቀኛል።*

*ጋዜጠኛ --- ለምንና እንዴት ብለው እርስዎን ምክር ይጠይቃሉ?*

*ዓይኔን በጨው --- አንተ ደግሞ ለምንና እንዴት ብለህ አትጠይቅ።*

*ጋዜጠኛ --- ይቅርታ አቶ ዓይኔን በጨው።*

ቀጥሏል ስጥ እንግዲሁ።  ወያኔና ማነታቸውን ቀይረውና ተቃዋሚ መስለው ያሉ ማፈሪያዎች ሁሉ ለምን በአሁኑ ጊዜ ኢሕአፓን ሊያራክሱ እንደ አበደ ውሻ ተቅበዘበዙ  በሚል ግራ የሚጋባ የለም። ተደናግሮም በቀጥታም ሆነ ባለማወቅ የሚያጅባቸው ካለ ግን ሊታዘንለት ይገባል። ዛሬ ለድርጅት ሳይሆን ለአቶ ኢያሱ ኢሳያስ ሳተላይት ቴሌቪዥን ሰጠው ለማለት ለምንስ አስፈለገ? የትኛውን የኢሕአፓ ጥረት ለማክሸፍና ድጋፍ ለማሳጣት ነው? መልሱ ከባድ አይደለም። አቶ ኢያሱ ከ 10 ዓመት በፊት ወደ አስመራ ሄደ አልሄደ ዛሬ ፋይድው ምንድነው? ከሻዕቢያ ተወዳጀ? ጦር ሰፈር በዚያ አቋቀመ? ተስፋዬ ጌታቸውን ገደላችሁ፣ ኮሎኔል ታደሰ ሙሉነህን አጠፋችሁ ወዘተ በሚል ማውገዙን አቆመ? ብዙ አቅጣጫ አስቀያሪ፣ የፈጠራ ክሶች እየተወረወሩ ነው።  የውሸት ክስ ፋብሪካዎቹ ሥራቸው ስለሆነ አይገርምም።  እኛም "ወግዱ! የጭቃ ውስጥ እሾሆች!" ካላልናቸው ደግሞ በየጊዜው ህዝባዊ ትግሉ ላይ ውሃ ለመከለስ መረባረባቸውን አያቆሙም። ጎበዝ በ 23 ዓመት ተመክሮ መንቃት ካልተቻለ ታዲያ መቼ?

ኢሕአፓ ላይ ነገር ከመጎንጎን ፣ ከመጠምጠም ማንበብ ከልብ ንሰሀ መግባት ለጎልማሶችም ለአረጋዊያንም የሚመከር ነው።።